የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሲፒርየር ፍርድ ቤት
የክለርክ (ጸሀፊ) ቢሮዎች አሰራሮች ማስታወቂያ
ኤፕሪል 6፣ 2020 የተሻሻለ

በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክኒያት ሁሉም የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የክለርክ (ጸሀፊ) ቢሮዎች ከርቀት (ሪሞት ስታተስ) ይሰራሉ፣ በፍርድ ቤቱ በአካል የሚገኝ ሰራተኛ አይኖርም። በቴሌፎን፣ ኢ-መይልና ቀጥታ ውይይት (ላይቭ ቻት) በመጠቀም ለጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የተዘጋጁ ሰራተኞች አሉን። ባለን ውሱን ሪሶርስስ ምክኒያት በፖስታ የሚላክልንን ሂደት ለማድረግ ስለምንቸገር፣ ለጥያቄዎ ምላሽ በመስጠት መዘግየት እንዳይኖር ለማድረግ እባክዎ ጥያቄዎን፣ ሰነድዎን ወይም የሰነድዎን ምስል በቴሌፎን ወይም በኢ-መይል ይላኩ። በክለርክ (ጸሀፊ) ቢሮዎች በርቀት ስለሚሰሩ ስራዎች መረጃ ከታች ይገኛል። ሁሉም አስቸኳይ ቀጠሮዎች (ሂሪንግስ) በዳኛ ከርቀት (ሪሞትሊ) ይካሄዳሉ። አስቸኳይ ቀጠሮ እንዲሰጥዎ ለመጠየቅ ሰነዶች ፋይል ሲያደርጉ እባክዎ የሁሉም አካላት የቴሌፎን ቁጥርና ኢ-መይል አድራሻ ያቅርቡ።

**የአስቸኳይ ጉዳዮች የተረጋገጡ (ሰርቲፋይድ) ቅጂዎች**

ኤለክትሮኒካዊ ሰርቲፋይድ ቅጂዎች የሚሰጡት መደበኛ አሰራሮች እስኪጀምር ድረስ ለአስቸኳይ ጉዳዮች ብቻ ነው። ሰርቲፋይድ ቅጂ ከፈለጉ ጥያቄዎን ለፍርድ ቤቱ ቢሮ ክለርክ (ጸሀፊ) በemergencycertifiedcopies@dcsc.gov ይላኩ። የጉዳይ (ኬዝ) ቁጥር፣ የቴሌፎን ቁጥርዎ እና ሰርቲፋይድ ቅጂ የሚያስፈልገው ድርጅት ስም፣ የመገናኛ መረጃ (ስም፣ ቴሌፎን ቁጥር እና ኢ-መይል አድራሻ) ጭምር ያካትቱ። ጥያቄዎ በተመለከተ ለማነጋገር ቢሮው ያገኝዎታል። በተጨማሪ፣ የቴሌፎን ቁጥር 202-879-1400 ለቢሮ በመደወል ጥያቄዎን ማቅረብ ይችላሉ።

**የኦዲተር ማስተር ቢሮ**

በኦዲተር ማስተር ላሉ ጉዳዮች ሰነዶች በኢ-መይል Auditor.Master@dcsc.gov መላክ ይችላሉ። ጉዳይዎ በተመለከተ ጥያቄ ቢኖርብዎ እባክዎ በቴሌፎን ቁጥር 202-626-3280 ያግኙን።

ለኦዲተር ማስተር ቢሮ ቀጠሮዎችና ሰነዶች ማምረት በተመለከተ ልዩ መረጃ ለማግኘት፣ በፍርድ ቤቱ ድረገጽ ያለውን ትእዛዝ እባክዎ ያንብቡ፡ https://www.dccourts.gov/sites/default/files/divisionspdfs/OAM-NOTICE-Cancelled-Hearings.pdf

**የፍትሐብሔር ክፍል (ሲቪል ዲቪዥን)**

የፍትሐብሔር ክፍል በኢ-ፋይሊንግ (eFiling) በኩል የተላኩ ሰነዶች ሂደት ማድረጉ ይቀጥላል። አስቸኳይ አቤቱታዎች ለግምገማ ወደ ዳኛ ይላካሉ።

1. ጠበቆችና ጠበቃ የሌላቸው ራሳቸው-የወከሉ ተከራካሪዎች ሰነዶችን በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በhttps://dc.casefilexpress.com/Login.aspx በሚገኘው ኬዝ ፋይል ኤክስፕረስ (Case File Express) በመጠቀም ፋይል ማድረግ ይችላሉ።

2. ኢ-ፋይሊንግ (eFiling) ማግኘት የማይችሉ ጠበቃ የሌላቸው ራሳቸው-የወከሉ ተከራካሪዎች አስቸኳይ አቤቱታዎችና ክፍያ አስቀድመው ላለመክፈል (የማመልከቻ ክፍያ ይተውልኝ) ማመልከቻ ማድረግ ቢፈልጉ፣ እንዚህን ሰነዶች ወደ Civilefilings@dcsc.gov በመላክ ፋይል ማድረግ ይችላሉ።

    a. የማመልከቻ ክፍያ ይተውልኝ ማመልከቻዎች በድረገጻችን https://www.dccourts.gov/services/judge-in-chambers/in-forma-pauperis-fee-waiver ይገኛሉ።

3. አስቸኳይ አቤቱታና የክፍያ ይተውልኝ ማመልከቻ  በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ማቅረብ የማይችሉ የቤት ጉዳይ ያለዎት ተከራይ ከሆኑ፣ ድጋፍ ለማግኘት ረይዚንግ ፎር ጀስቲስ (ለፍትህ መነሳት) የተባለው ድርጅት ከሰኞ እስከ አርብ ከ9፡00 ኤ.ኤም. እስከ 5 ፒ.ኤም. በ202-638-4798 ማግኘት ይችላሉ።

4. አስቸኳይ አቤቱታና የክፍያ ይተውልኝ ማመልከቻ  በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ማቅረብ የማይችሉ የአከራይና ተከራይ ጉዳይ ያለዎት ከሆነ ድጋፍ ለማግኘት ለሚከተሉትን ማግኘት ይችላሉ፡

    a. ዲ.ሲ. ባር ፕሮ ቦኖ ማእከል - የአከራይና ተከራይ ሀብት ማእከል ጊዝያዊ የቴሌፎን መስመር 202-780-2575

5. የሸማቾች ህግ (ኮንሱመር ሎው) ሀብት ማእከል ትናንሽ የይገባኛል ጥያቄዎች ጉዳዮች፣ ዕዳ መሰብሰብ፣ የኪራይ ቀብድ ማስመለስ (ረንት ዲፖዚት ሪካቨሪ)፣ እና ሌላ የሸማቾች ጉዳዮች በተመለከተ መረጃ ያቀርባል። እንደነ በባንክ ሂሳብዎ የተያያዘ ነገር የመሳሰሉትን በሸማቾች ጉዳዮች አስቸኳይ ነገር ቢኖርብዎ፣ እና አስቸኳይ አቤቱታና የክፍያ ይተውልኝ ማመልከቻ  በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ማቅረብ የማይችሉ ከሆነ የሚከተለውን የቴሌፎን ቁጥር መደወል ይችላሉ፡

    a. ዲ.ሲ. ባር ፕሮ ቦኖ ማእከል - የሸማቾች ህግ (ኮንሱመር ሎው) ሀብት ማእከል ጊዝያዊ የቴሌፎን መስመር 202-780-2574።

እባክዎ የሚመለከታቸው የክለርክ (ጸሀፊ) ቢሮዎች በሚከተሉት የቴሌፎን ቁጥሮች በመደወል ወይም በድረገጹ በቀኝ በኩል በሚገኝ ቀጥታ ውይይት (ላይቭ ቻት) በሚል አዝራር (ባተን) በመጫን ያግኙ።

*የፍትሐብሔር እርምጃ (ሲቪል አክሽን) ቅርንጫፍ፡*
202-879-1133
ቀጥታ ውይይት (ላይቭ ቻት)፡ https://www.dccourts.gov/services/civil-matters/requesting-over-10k

*የአከራይና ተከራይ ቅርንጫፍ፡*
202-879-4879
ቀጥታ ውይይት (ላይቭ ቻት)፡ https://www.dccourts.gov/services/civil-matters/landlord-tenant

*የአነስተኛ ይገባኛል (ስሞል ክሌይምስ) ቅርንጫፍ፡*
202-879-1120
ቀጥታ ውይይት (ላይቭ ቻት)፡ https://www.dccourts.gov/services/civil-matters/requesting-10k-or-less

LIVE CHAT
Got a Question? Let us help

**የወንጀል ሰለባዎች ካሳ ፕሮግራም**

ሁሉም ከወንጀል ሰለባዎች ካሳ ፋንድ ለማግኘት የሚደረጉ ማመልከቻዎች በሰራተኞች በርቀት ሂደት ይደረጋሉ። አዳዲስ ማመልከቻዎች ወደ CVCPapplications@DCSC.gov በኢሜይል መላክ ይችላሉ፣ ወይም በኦንላይን ተሞልተው ለቢሮው በቅጹ መጨረሻ ባለው ያስረክቡ (ሳብሚት-submit) የሚለውን አዝራር (ባተን) በመጫን ማስረከብ ይቻላል።

የወንጀል ሰለባዎች ካሳ ማመልከቻ በፍርድ ቤቱ ድረገጽ ይገኛል https://www.dccourts.gov/sites/default/files/CVCPApplicationMarch2020.pdf።

ማመልከቻው በኦንላይን ማጠናቀቅ የማይችሉ ከሆነ አዲስ እና ነባር የይገባኛል ጥያቄዎች እርዳታ ለማግኘት ቢሮውን በቴሌፎን ቁጥር 202-879-4216 ወይም በኢሜይል CVCPOffice@dcsc.gov ማግኘት ይችላሉ።

**የወንጀል ክፍል**

የፍርድ ቤት ጉዳዮች ዝርዝር (ኮርት ዳኬት) እና አንዳንድ ሰነዶች በኦንላይን መደረግ ይችላሉ። በተጨማሪ፣ የመቀጮ እና ማካካሻ ክፍያዎች በኦንላይን መደረግ ይችላሉ። ሰነዶች የሚታይበትና ክፍያ የሚፈጸምበት ድረገጽ https://eaccess.dccourts.gov/eaccess ነው። የቦንድ ክፍያዎች በተመለከተ ጥያቄዎች ቢኖርብዎ ከቢሮው ጋር ይገናኙ።

ጥያቄዎች ቢኖርብዎ እባክዎ የወንጀል ክፍል ክለርክ (ጸሀፊ) ቢሮ በቴሌፎን ቁጥር 202-879-1373 ወይም በኢሜይል CriminalCaseManagement@dcsc.gov ያግኙ።

**የቤት ውስጥ ብጥብጥ ክፍል (ዶመስቲክ ቫዮለንስ ዲቪዥን)**

በድንገተኛ አደጋ ላይ ካሉ 911 ወይም ዲ.ሲ. ሴፍ ክሪቲካል ሪስፖንስ ቲም (ወሳኝ ምላሽ ሰጪ ቡድን) በ(800) 407- 5048 በመደወል በአስቸኳይ መከላከያ ትእዛዝ ሂደት በኩል ጊዝያዊ መከላከያ ትእዛዝ (ቲ.ፒ.ኦ.) መጠየቅ ይችላሉ። አስቸኳይ ቲ.ፒ.ኦ. ለሰባት ቀናት በቀን ለ24 ሰአታት ያህል ይገኛል። የቤት ውስጥ ብጥብጥ (ዲ.ቪ.) ማእከሎች ዝግ ናቸው፣ ነገር ግን በዲ.ሲ. ሴፍ ክሪቲካል ሪስፖንስ ቲም (ወሳኝ ምላሽ ሰጪ ቡድን) በኩል አገልግሎት ከሚሰጡ ጋር መገናኘት ይችላሉ።

በተጨማሪ፣ ቲ.ፒ.ኦ. እና ሌሎች አስቸኳይ አቤቱታዎችና ጥያቄዎች በwww.probono.net/dccourts በኩል ፋይል መደረግ ይችላሉ። አስቸኳይ ጥያቄዎች በፍትህ ኦፊሰር ለውሳኔ በርቀት ይገመገማሉ። እባክዎ ቅጾቹ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ አጠናቀው ያስረክቡ፣ በመቀጠል ፋይል ማድረጉ ለመጨረስ የክለርክ (ጸሀፊ) ቢሮ በቴሌፎን ቁጥር (202) 879-0157 ይደውሉ ወይም በdomesticviolencemanagement@dcsc.gov ኢሜይል ይላኩ።

በተጨማሪ፣ ቅጾች በዲ.ሲ. ፍርድ ቤት ድረገጽ በhttp://www.dccourts.gov/services/forms?title=&combine ይገኛሉ።

ጥያቄዎች ቢኖርብዎ የዲ.ቪ. ክለርክ (ጸሀፊ) በቴሌፎን ቁጥር 202-879-0157 ወይም በኢሜይል domesticviolencemanagement@dcsc.gov ያግኙ።

**የቤተሰብ ፍርድ ቤት (ፋሚሊ ኮርት)**

የቤተሰብ ፍርድ ቤት በኢፋይሊንግ (eFiling) በኩል የተላኩ ሰነዶች ሂደት ማድረጉ ይቀጥላል። አስቸኳይ አቤቱታዎች ለግምገማ ወደ ዳኛው ይላካሉ፣ ሁሉም ቀጠሮዎች በርቀት ይካሄዳሉ።

1. ጠበቆችና ጠበቃ የሌላቸው ራሳቸው-የወከሉ ተከራካሪዎች ሰነዶችን በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በhttps://dc.casefilexpress.com/Login.aspx በሚገኘው ኬዝ ፋይል ኤክስፐረስ (Case File Express) በመጠቀም ፋይል ማድረግ ይችላሉ።

2. ጠበቃ የሌላቸው ራሳቸው-የወከሉ አስቸኳይ ጉዳይ ፋይል ማድረግ የሚፈልጉ ተከራካሪዎች ራስ-አግዝ ማእከል (ሰልፍ ሄልፕ ሰንተር) በ202-879-0096 ያግኙ።

ጥያቄዎች ቢኖርብዎ እባክዎ የቤተሰብ ፍርድ ቤት የጥሪ ማእከል (ኮል ሰንተር) በቴሌፎን ቁጥር 202-879-1212 ያግኙ።

*የጋብቻ ቢሮ*

ፍርድ ቤቱ ከመዘጋቱ በፊት (በኮቪድ-19 ምክኒያት) የፍትሐብሔር ጋብቻ (ሲቪል ዌዲንግ) ለማድረግ ቀጠሮ ይዘው ለነበሩ ሁሉም አካላት የጋብቻ ምስክር ወረቀታቸውን ወደ ጋብቻቸው ራሳቸው ይፋ ለማድረግ (ሰልፍ ኦፊሽየት)፣ ወይም ጋብቻቸው ፈቃድ ባለው የሀይማኖት ወይም ፍትሐብሔር ስነ ስርአት በሚያደር እንዲያደርጉ ለማስታወቅ የጋብቻ ቢሮ ለሁሉም አካላት አግኝቷል።

በዚህ ሰአት፣ የጋብቻ ምስክር ወረቀት የሚሰጠው ለአስቸኳይ ጉዳዮች ብቻ ነው፣ ይህም በርቀት አሰራር ነው የሚሰጠው። የጋብቻ ምስክር ወረቀት ለመጠየቅ እባክዎ ለፍርድ ቤቱ ክለርክ (ጸሀፊ) ቢሮ በemergencycertifiedcopies@dcsc.gov ኢሜይል ይላኩ፣ ወይም በስልክ ቁጥር 202-879-1400 ያናግሩ።

**የጁሮርስ ቢሮ (ጁሮርስ ኦፊስ)**




ጁሮሮች በኦንላይን በwww.dccourts.gov/jurorservices በኩል የጁሮሮች መጠይቅ ማጠናቀቅ፣ የጁሪ ግዴታ አገልግሎት ማስተላለፍ፣ እና ከጁሪ ግዴታ አገልግሎት እንዲተዉ መጠየቅ ይችላሉ። ጁሮሮች በተጨማሪ የተጠናቀቀ መጠይቃቸው ወይም የተጠናቀቀ መጠይቃቸው ምስል ለjurorhelp@dcsc.gov በኢመይል መላክ ይችላሉ።

የጁሮር ቢሮ በቴሌፎን በ202-879-4604፣ በኢመይል በjurorhelp@dcsc.gov ወይም በድረገጹ https://www.dccourts.gov/jurors/about-your-jury-duty በቀኝ በኩል በሚገኘው ቀጥታ ውይይት (ላይቭ ቻት) የሚለውን አዝራር (በተን) በመጫን፣ ከሰኞ እስከ አርብ ከ8:30 ኤ.ኤም. - 5፡00 ፒ.ኤም. ጥያቄዎች ለመመለስ ዝግጁ ነው።

**የኑዛዜ ወይም ውርስ ህጋዊነት ማረጋገጫ ክፍል (ፕሮቤት ዲቪዥን)**

የኑዛዜ ወይም ውርስ ህጋዊነት ማረጋገጫ ክፍል (ፕሮቤት ዲቪዥን) በኢፋይሊንግ (eFiling) በኩል የተላኩ ሰነዶች ሂደት ማድረጉ ይቀጥላል። አስቸኳይ ጉዳዮች (21-ቀን እና ጊዜያዊ ሞግዚትነት) ለግምገማ ወደ ዳኛ ይላካሉ፣ ሁሉም ቀጠሮዎች በርቀት ይካሄዳሉ። በተጨማሪ፣ ቀጠሮ ለማያስፈልጋቸው አስቸኳይ-ላልሆኑ ጉዳዮች ዳኞች ውሳኔ ይሰጣሉ።

1. ጠበቆችና ጠበቃ የሌላቸው ራሳቸው-የወከሉ ተከራካሪዎች ሰነዶችን በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በhttps://dc.casefilexpress.com/Login.aspx በሚገኘው ኬዝ ፋይል ኤክስፕረስ (Case File Express) በመጠቀም ፋይል ማድረግ ይችላሉ።

2. ጠበቃ የሌላቸው ራሳቸው-የወከሉ በኬዝ ፋይል ኤክስፕረስ (Case File Express) በኩል ኢፋይል (eFiling) ማድረግ የማይችሉ ተከራካሪዎች፣ ለአስቸኳይ ጉዳይ ሰነዶች በኢመይል አድራሻ ProbateEmergencyFilings@dcsc.gov በመላክ ፋይል ማድረግ ይችላሉ።

    a. የፍርድ ቤት ክፍያዎች አስቀድሞ መክፈሉ (ፕሪፐይመንት ኦፍ ኮስትስ) ይተውልኝ ብለው መጠየቅ የሚፈልጉ ከሆነ፣ እባክዎ በድረገጻችን ያለው የክፍያ ይተውልኝ ማመልከቻ ይሙሉ፡ https://www.dccourts.gov/services/judge-in-chambers/in-forma-pauperis-fee-waiver

3. **የአስቸኳይ ጉዳይ** አቤቱታ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ ማቅረብ የማይችሉ ከሆነ፣ ለፕሮቤት አስቸኳይ ፋይሊንግ የቴሌፎን መስመር በ202-879-9436 ማግኘት ይችላሉ።

4. በተጨማሪ፣ አስቸኳይ-ላልሆኑ ጉዳዮች ሰነዶች በፖስታ ወደ D.C. Superior Court Probate Division, 515 5th Street, N.W. Washington, DC 20001. Attention: Probate Clerk's Office መላክ ይችላሉ።

ለአስቸኳይ ጉዳይ አቤቱታ እንዴት ማድረግ እንዳለብዎት ልዩ መመሪያዎች ከፈለጉ እባክዎ የፕሮቤት ክፍል ድረገጽ https://www.dccourts.gov/services/probate-matters ይመልከቱ።

የፕሮቤት ክፍልን ከቴሌፎን ቁጥሮቻቸው ባንዱ ቁጥር በመደወልና መልእክት በመተው፣ ኢሜይል በመላክ፣ ወይም በድረገጹ በቀኝ በኩል በሚገኘው ቀጥታ ውይይት (ላይቭ ቻት) የሚለውን አዝራር (በተን) በመጫን ማግኘት ይቻላል።




የኑዛዜን ወይም ውርስን ህጋዊነት ማረጋገጥ (ፕሮቤት) አጠቃላይ ጥያቄዎች
ቴሌፎን፡ 202-879-9460 ወይም 202-879-9461
ኢሜይል፡ Probateinquiries@dcsc.gov
ልዩ የሞግዚትነት ጥያቄዎች
ኢሜይል፡ GuardianshipAssistanceProgram@dcsc.gov።
ቀጥታ ውይይት (ላይቭ ቻት)፡ https://www.dccourts.gov/services/probate-matters

**የታክስ (ግብር) ክፍል**
ጠበቆችና ጠበቃ የሌላቸው ራሳቸው-የወከሉ ተከራካሪዎች ሰነዶችን በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በhttps://dc.casefilexpress.com/Login.aspx በሚገኘው ኬዝ ፋይል ኤክስፕረስ (Case File Express) በመጠቀም ፋይል ማድረግ ይችላሉ። ከዚህም በተጨማሪ፣ ጠበቃ የሌላቸው ራሳቸው-የወከሉ ተከራካሪዎች ማመልከቻዎቻቸው (ፒቲዲንግስ) ወይም የማመልከቻዎቻቸው (ፒቲዲንግስ) ምስል በኢሜይል አድራሻ TaxDocket@dcsc.gov በመላክ ፋይል ማድረግያ ክፍያቸው ደግሞ በቼክ ወይም ማኒ ኦርደር ለD.C. Superior Court, Tax Division, 500 Indiana Ave., NW, Suite 4100, Washington, DC 20001 መላክ ይችላሉ።

ጥያቄዎች ቢኖርብዎ ለታክስ (ግብር) ክፍል በቴሌፎን ቁጥር 202-879-1737 ወይም በኢሜይል TaxDocket@dcsc.gov ያግኙ።

*በተጨማሪ፣ ጥያቄዎች ቢኖርብዎ ለሱፒርየር ፍርድ ቤት ክለርክ (ጸሀፊ) በቴሌፎን ቁጥር 202-879-1400 ማግኘት ይቻላል።*

[**ተፈርሞበታል**]

*ዛብሪና ዴምፕሰን*

*የሱፒርየር ፍርድ ቤት ክለርክ (ጸሀፊ)*